## ሬኒየር ቫሊ የዝናባማ ወቅት ክምችት ፕሮጀክት መረጃ

### ቆሻሻ ፍሳሽ ምንድን ነው?

ቆሻሻ ፍሳሽ ማለት ማንኛውም ከአንድ ህንፃ የእጅ መታጠቢያ እና እቃ ማጠቢያ፣ ሻወር፣ ገንዳ ወይም መጸዳጃ የሚወጣ ነገር ነው።። ይህ ቆሻሻ ሁሉ በአንድ ላይ ተጠራቅሞ አንድ በጣም የቆሸሸ ውሃ ጅረት ይፈጥራል ይሄም ቆሻሻ ፍሳሽ ተብሎ ይጠራል።

ከቆሻሻ ፍሳሽ ጋር ንክኪ ለበሽታ ሊያጋልጠን ይችላል።ቆሻሻ ፍሳሽን ከሰዎች ማራቅ ጤንነታችንን ለመጠበቅ ይረዳል። ቆሻሻ ፍሳሽ ካልተጸዳ ሂደት የፒዩጅት ሳውንድ ሃይቆችን እና ወንዞችን ሊያበላሽ/ ሊጎዳ ይችላል።

### የጎርፍ ውሃ ምንድን ነው?

የጎርፍ ውሃ ማለት ሃይለኛ ዝናብ ጊዜ ከእግር መንገድ፣ ከመኪና አስፋልት፣ ከጣሪያዎች እና በውጭ ከሚገኙ ሥፍራዎች የሚፈስ ውሃ ነው። የሞተር ዘይት፣ ጋዝ፣ የእንስሳት እዳሪ፣ የአትክልት ማዳበሪያ፣ የትንኝ ማጥፊያ መርዝ፣ የቤት ቆሻሻ እና ሌሎች ሌሎች ኬሚካሎች ወደ ውጭ ይጣላሉ። እነዚህ ሁሉ መድረሻቸው የጎርፍ ውሃ ይሆናል።

የጎርፍ ውሃ ጋር ንክኪም ለበሽታ ሊያጋልጠን ይችላል። የጎርፍ ውሃም ካልተጸዳ በጊዜ ሂደት የፒዩጅት ሳውንድ ሃይቆችን እና ወንዞችን ሊያበላሽ/ ሊጎዳ ይችላል።

በአዳዲስ ከተማዎች የጎርፍ ውሃ በተቀበረ የምድር ሥር ቱቦ በመንገድ መታጠፊያዎች እያደረገ ይፈስሳል። ይሄ ቱቦ የጎርፉ ውሃ በጥንቃቄ እንዲጣራ የቆሻሻ ፍሳሽ ወደሚገባበት ማጣሪያ ሥፍራ ይወስደዋል። እንደ ሲያትል ያሉ በቆዩ ከተሞች የጎርፍ ውሃ እና የቆሻሻ ፍሳሽ የሚፈሰው በአንድ ቱቦ ነው።

### ኪንግ ካውንቲ የጎርፍ ውሃ እና የቆሻሻ ፍሳሽን ለማጣራት ምን ያደርጋል?

ሁሉም ህንፃ ቆሻሻ ፍሳሽን የሚያስወግድበት የራሱ የሆነ ቱቦ አለው። ቆሻሻ ፍሳሹም ከእነዚህ ቱቦዎች ወደሚተልቅ ባለቤትነቱ በኪንግ ካውንቲ ወደሆነ ቱቦ ውስጥ ይገባል። የካውንቲው ቱቦ ቆሻሻ ፍሳሹን በጥንቃቄ ተጣርቶ ወደ ፒዩጅት ሳውንድ የሚሄድበት ማጣሪያ ይወስደዋል። በሬኒየር ቫሊ የጎርፍ ውሃ ወደ ማጣሪያው የሚገባበት ቱቦ ራሱ ለቆሻሻ ፍሳሽ የሚጠቀመውን ነው።

ኪንግ ካውንቲ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ የሚጣራበትን የማጣሪያ ሥፍራ ያስተዳድራል። የተጣራውም ውሃ ወደ ፒዩጅት ሳውንድ (ወይም በካርኔሽን አቅራቢያ ወዳለው ወደ ቶልት ወንዝ) ይላካል። በኪንግ ካውንቲ አቅራቢያ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ የሚጣሩባቸው ስድስት ማጣሪያዎች አሉ። የሬኒየር ቫሊ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ በቢከን ሂል ሥር በሚያልፉ ቱቦዎች አድርጎ ከዱዋሚሽ ወንዝ እና ሲያትል ዋተርፍሮንት ጋር ማንጎሊያ ወደሚገኝ ማጣሪያ ይፈሳል።

### ኪንግ ካውንቲ ምን እየገነባ ነው?

ኪንግ ካውንቲ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ ወደድዋሚሽ ወንዝ እንዳይገባ የሚያግድ አዲስ ቱቦ እና ማጠራቀሚያ ገንዳ በመገንባት ላይ ይገኛል።

### አዲሱ ቱቦ እንዴት አድርጎ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ ውሃን ወደድዋሚሽ ወንዝ እንዳይገባ የማገድ ይችላል?

በሀይለኛ ዝናብ ጊዜ እጅግ ብዙ የሆነ የጎርፍ ውሃ ከሬኒየር ቫሊ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ በሚወስዱት ቱቦዎች ወደ ኪንግ ካውንቲ ማጣሪያ ይገባል። እነዚህ ቱቦዎችም ይሞላሉ: ይህም ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ ውሃ ከካውንቲው ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ እንዲፈስ ያደርጋል።

ከሬኒየር ቫሊ ካውንቲ ትልልቅ ቱቦዎች አንዱ በደቡብ ሬኒየር አቬኑ (Ave. S.) እና በደቡብ ማርቲን ሉተር ኪንግ ዌይ (S) ሥር ያልፋል። አዲሱ ቱቦ ይህንን ትልቅ ቱቦ በደቡብ ሬኒየር አቬኑ (Ave. S.) አድርጎ በደቡብ ቤቪው መንገድ (S. Bayview St.) ሥር ከሚሄድ ሌላ ቱቦ ጋር ያገናኘዋል። ሁለቱን ቱቦዎች ማገናኘት ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ ውሃን ከሞላው ቱቦ ወጥቶ በደቡብ ሬኒየር አቬኑ (Ave. S.) አድርጎ እንዲሄድ ያደርጋል።

### አዲሱ ገንዳ እንዴት አድርጎ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ ውሃን ወደ ድዋሚሽ ወንዝ እንዳይገባ የማገድ ይችላል?

ይሄው ትልቅ የካውንቲው ቱቦ በደቡብ ሬኒየር አቬኑ(Ave. S.) አድርጎ ወደ ኮሎምቢያ ከተማ እየተጠጋ ሲሄድ በማርቲን ሉተር ኪንግ ዌይ (S) ሥር ይሄዳል። በደቡብ ሃንፎርድ መንገድ (S) ሥር ከሚሄደው በሃይለኛ ዝናብ ወቅት ከሚሞላው ቱቦ ጋር ይገናኛል። በደቡብ ሃንፎርድ መንገድ (S) ቱቦ ሲሞላ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ ውሃ ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ እንዲፈስ ያደርጋል። እነዚህ ፍሳሾች ኮምባይንድ ሱወር ኦቨርፍሎው (Combined Sewer Overflows) ወይም ሲኤስኦ ይባላሉ።

ገንዳው የተረፈው ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ ወደ ዱዋሚሽ ወንዝ ከመፍሰሱ በፊት ያጠራቅመዋል። ሃይለኛው ዝናብ ሲያቆም በገንዳው ያለው ቆሻሻ ፍሳሽ እና የጎርፍ ውሃ በደቡብ ሃንፎርድ መንገድ (S) ሥር ወደሚያልፈው ቱቦ ገብቶ ማንጎሊያ በሚገኘው ማጣሪያ ይጣራል።

### ኪንግ ካውንቲ ይህን ቱቦ እና ገንዳ መገንባት ለምን አስፈለገው?

ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ የጎርፍ ውሃን ከዱዋሚሽ ወንዝ ማስወገድ ጤናችን እንዲጠበቅ እና ወንዙም ንፁህ እንዲሆን ይረዳል።

የከተማው ህግ በደቡብ ሃንፎርድ መንገድ (S) ሥር ከሚያልፈው ቱቦ የሚወጣው ፍሳሽ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሆን ይደነግጋል። የዩ.ኤስ. አካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ የኪንግ ካውንቲን ሲኤስኦ ፍሳሽ በ 2030 ዓ.ም. በዓመት ወደአንዴ እንዲቀንስ የይጠይቅበታል። በዱዋሚሽ ወንዝ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎችም የዱዋሚሽ ሲኤስኦ በመጀመሪያ እንዲፀዳ ጠይቀዋል።ኪንግ ካውንቲም የዱዋሚሽ ወንዝ ላይ ነዋሪዎች በጠየቁት መሰረት ሥራ ጀምሯል።

### ኪንግ ካውንቲ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ የጎርፍ ውሃን ከዱዋሚሽ ወንዝ ለማስወገድ የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች እንዴት ወሰኖ መረጠ?

ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ የጎርፍ ውሃን ከወንዙ ለማስወገድ መጠቀም የሚቻሉ የተለያዩ መሳሪያዎች አሉ። ሁሉም ዓይነት መሳሪያዎች ለሁሉም አይነት መንደሮች አይሆኑም። ኪንግ ካውንቲ አዲስ ቱቦ እና ገንዳ እንዲገነባ ከመጠየቁ በፊት የፕሮጀክቱ ቡድን ምን ዓይነት መሳሪያዎች በአንደኛ ደረጃነት መጠቀም እንዳለበት አስቦበት ነበር።

ሬኒየር ቫሊ አገልግሎት ሰፊ በጣም ብዙእንቅስቃሴ ያለበት፡ ብዙ ሰዎች የሚኖሩበት እና የሚሠሩበት አካባቢ ላይ መሆን አለበት። ህብረተሰቡን በትክክለኛው መንገድ ለመርዳት ሬኒየር ቫሊ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሷል፥

- የትኞቹ መሳሪያዎች በአንደኝነት አስተማማኝ ናቸው?
- የትኞቹ የካውንቲው ቱቦዎች እና ፓምፖች ሊረዱ ይችላሉ?
- ግልጋሎት መስጫውን በተቻለ አቅም እንዴት ማሳነስ ይቻላል?
- የትኞቹ መሳሪያዎች ወጪን ይቆጥባሉ?
- ግልጋሎት መስጫው እንዴት በመንደሩ ውስጥ በቂ በሆነ ሥፍራ ላይ ማረፍ ይችላል?

የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች ኪንግ ካውንቲን አዲስ ቱቦ እንዲጨምር፣ አንዳንድ የድሮ ቱቦዎችን እንዲጠግን እና አዲስ ገንዳ እንዲሰራ እንዲወስን ረድተውታል። እነዚህ መሳሪያዎች ኪንግ ካውንቲ ቆሻሻ ፍሳሽ እና የተበከለ የጎርፍ ውሃን ከዱዋሚሽ ወንዝ በጥንቃቄ እና በአስተማማኝ መንገድ ለማስወገድ ይረዳሉ። የእነዚህ ተቋሞች/ሥፍራዎች ግንባታ ለመኪናዎችን እና ለመንደሮች የማያስቸግር ሁኔታን ያመቻቻል። ለመሥራትም ጥቂት ንብረትን ብቻ ስለሚጠይቁ መንደሩ ተጨማሪ የሥራ፣ የገበያ እና የመኖሪያ ቦታዎችን ለመጨመር ያስችላል።

### ለመሥራት ምን ያህል ጊዜ ያስፈልገዋል?

ፕሮጀክቱ ሁለት አመት የሚፈጅ ሲሆን በ2017 ፎል ላይ ይጠናቀቃል።

**ሲጠናቀቅ ምን ይመስላል?**

የደቡብ ቤቪው መንገድ (S. Bayview St.) ቱቦ በምድር ሥር ስለሚሆን ንብረቶቹ ሁሉ አሁን ያላቸውን መልክ አይለቁም።

የደቡብ ሃንፎርድ መንገድ (S) ገንዳም በምድር ሥር ይሆናል። አንዳንድ መሳሪያዎቹ ከምድር በላይ ሲሆኑ በባለ አንድፎቅ ህንፃ ውስጥ ይሆናሉ። በገንዳው እና ህንፃው ዙሪያ አጥር ይታጠራል። ቦታው ይስተካከላል። በቦታው ዙሪያም የመንገድ መሻሻል ይደረጋል።

**ኪንግ ካውንቲ በግንባታው እንዲረዱ ሰዎችን ይቀጥራል?**

ኪንግ ካውንቲ በቂ ሙያ ያለው የግንባታ ሠራተኛ እነዚህን መገልገያዎች ለመስራት ይቀጥራል። ስለ ኪንግ ካውንቲ ሥራዎች በተጨማሪ ለማወቅ እባክዎን ይህን ድህን ይጎብኙ፥ http://www.kingcounty.gov/jobs.aspx

**ኪንግ ካውንቲ የግሊጋሎት መስጫውን ለመገንባት ማንን እንደሚቀጥር እንዴት ይወስናል?**

ኪንግ ካውንቲ የሚቀጥረው የግንባታ ሰራተኛ ኪንግ ካውንቲ ለሚያወጣው እና ለሚያወዳድረው ጨረታ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። የጨረታው መረጃ በ kingcounty.gov ላይ በ 2015 ዓ.ም. ያገኛሉ።

**የግሊጋሎት መስጫው ለእኔ ችግር የሚፈጥር ከሆነስ?**

ኪንግ ካውንቲ እና የፕሮጀክቱ ቡድን የህብረተሰቡ አባላት ሃሳባቸውን፣ አይታቸውን እና አስተያየት እንዲያካፍሏቸው ይፈልጋሉ። ስለፕሮጀክቱ ቅሬታ ቢኖርዎት ችግር የለውም። ኪንግ ካውንቲ የግሊጋሎት መስጫው ለመንደሩ በአግባቡ የሚመጥን ለማረግ ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ ይሰራል። ስለፕሮጀክቱ ቅሬታ ቢኖርዎት እርስዎንም ሆነ ህብረተሰቡን የሚነካበት ሁኔታ ካለ እባክዎ ያሳውቁን።

**የግሊጋሎት መስጫው ሲገነባ ለእኔ ችግር የሚፈጥር ከሆነስ?**

ኪንግ ካውንቲ መልካም ጎረቤት ሊሆን ይፈልጋል። ከግንባታ አጠገብ መኖር አሰልቺ እና አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። በግንታው ወቅት ኪንግ ካውንቲ ፕሮጀክቱን በተመለከተ ከህብረተሰቡ አባላት ጋር አንድ ለ አንድ የሚሰሩ ሰራተኞች ይኖራሉ። ኪንግ ካውንቲ ስለፕሮጀክቱ መረጃ በየጊዜው በኢሜልም ሆነ በቀጥታ በቤትዎ በር ላይ ይሰጥዎታል። ነፃ የፕሮጀክት ሆትላይንም በቀንና በምሽት የፕሮጀክቱን ቡድን አባል ማግኘት ለሚፈልጉ ለህብረተሰቡ አባላት ዝግጁ ይሆናል (206-205-9178)። አስፈላጊ ከሆነም ኪንግ ካውንቲ አስተርጓሚ በነፃ ሊመድብ ይችላል።